# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የሕንጻ ፈንድ ማሰባሰብ ፕሮግራም

ለሕንጻ ግዢ ለመስጠት ቃል የገባነውን ገንዘብ በገባችሁት ቃል መሰረት የፈጸማችሁ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ለመስጠት ቃል የገባችሁ ደግም ስጦታውን እስከ አመቱ መጨረሻ (ወይንም ቃል በገባነው መሰረት) እንድንሰጥ እናበረታታችኋለን። የህንጻ ኮሚቴ አስተባባሪዎች።

### የአዲስ አመት ፕሮግራም

የችካጎና አካባቢው አብያተ ክርስቲያናት በብረሃነ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን በአንድነት ማዕድ በመቁረስ፣ በጸሎት፣ በአምልኮ፣ ቃሉን በመካፈልና በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች የአዲስ አመት ማዜማ ፕሮግራምን በጋራ ያካሂዳሉ። ሁላችንም በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንሁን።

### የጾምና የጸሎት ፕሮግራም

በቤተ ክርስቲያን የታወጀው የጾምና የጸሎት ፕሮግራም በDecember 26, 27, እና 28 ከሰአት ከ12፡30 ጀምሮ እስከ 3፡00 ድረስ እንዲሁም በDec. 29 (አርብ) በመደበኛ ፕሮግራማችን ጊዜ ይካሄዳል። በዚህ የጾም ጸሎት ፕሮግራም የምንችል ሁሉ እንድንካፈል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች።

"ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ሲሳይ)
773-865-6102 (ብረሃኑ)
773-507-0194 (ጋሽ አያሌው)
773-910-0485 (ፒተር)
773-961-5332 (ጌቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10



"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል"
(ያዕ. 4፡6)

Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625

መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

**December 17, 2017**

**ታኅሣሥ 8፣ 2010 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................. | ወንድም ጌቱ ጳውሎስ |
| አምልኮ....................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ጌቱ ጳውሎስ |
| ቃል ............................ | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ ጸልዩም፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች፥ ሥጋ ግን ደካማ ነው…”

(ማር. 14፡38)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመጎ | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### ጸሎት አስተምረን -- ወደ ፈተና አታግባን (ክፍል አስራ-አራት)

*“እርሱም በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር፥ በጨረሰም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፦ ጌታ ሆይ... እንጸልይ ዘንድ አስተምረን አለው። አላቸውም፦ ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፦ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ... <u>ወደ ፈተና አታግባን</u>።” (ሉቃ. 11፡4)*

ጌታችን ባስተማረን ጸሎት ውስጥ አንዱ የምናቀርበው ልመና እግዚአብሔርን ሆይ ወደ ፈተና አታግባን የሚል ነው። በዚህ አውድ ውስጥ “ፈተና” ተብሎ የተገለጸው ሃሳብ በእንግሊዘኛ “temptation” የተባለው ሃሳብ ነው። ይህም ወደ ኃጢያት የሚመራ ፍላጎት ነው። ሐዋሪያው ያዕቆብ እንደሚያስተምረን የምንፈተነው በገዛ ምኞታችን ስንሳብና ስንታለል ነው። (ያዕ. 1፡14) ከዚያም በኋላ ምኞት ጸንሳ ኃጢያትን ትወልዳለች። የኃጥያትም ፍሬ ወይንም ውጤት ሞት ነው። (ቁ. 15) የውድቀትን ሰንሰለት ስንመለከት ጅማሬው በምኞት ተስቦ መታለልና መፈተን ነው። ፈተናው ካልጨነገፈ ወደ ኃጢያት ያመራል። ኃጢያት ደግሞ ሞትን መውለዱ የማይቀር ነው። በውድቀታችንም የሆነው ይኼው ነው። በመጀምሪያ ሰው በሰይጣን ማታለል ተስቦ ተፈተነ። ከዚያም ተፈተነ። ፈተናውንም ማለፍ ተስኖት በኃጢያት ወደቀ። ኃጢያትም የዘላለምን ሞት አመጣብን።

ስለዚህ ጉዳይ ጌታችን በሌሎች ስፍራዎችም ከጸሎት ጋር አገናኝቶ ሐዋሪያቱን አስተምሯል። ለምሳሌ በማቴዎስ 26፡41 ላይ “ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ” ብሏል። እንዲሁም በማርቆስ 14፡38 ላይ “ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ ጸልዩም” ብሏል። ከነዚህ ክፍሎች የምረዳው ሃሳብ ወደ ፈተና እንዳንገባ በጌታ ፊት ጸጋን መጠየቅ እንዳለብን ነው። በእግዚአብሔር ፊት መጸለይ በእግዚአብሔር ሃሳብ ውስጥ እንድንኖርና ወደ ፈተናም እንዳንገባ ጸጋን ያበዛልናል። እናስታውስ “ወደ ፈተና አታግባን” ብለን ስንጸልይ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ የፈተናችን ምንጭ እንደሆነ ማለታችን ሳይሆን እርሱ ወደ ፈተና እንገባ ዘንድ እንዳይተወን (ጥበቃውን ከኛ እንዳያነሳ) መጸለያችን ነው። የፈተና ምንጭ የራሳችን ክፉ ምኞት እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። ስለዚህም ሐዋሪያው ያዕቆብ እንዲህ ይመክረናል። “ማንም ሲፈተን፦ በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም።” (ያዕ. 1፡13)

ከዚህ ጸሎት አንጻር አንድ ተጨማሪ ሃሳብ መረዳት አለብን። ጸሎቱ መከራ ከምንለው የፈተና አይነት (trial or suffering) ጋር የተገናኘ አይደለም። ክርስቲያኖች እምነታችን ሊፈተን ይችላል። በእምነታችን መፈተን ሲገጥመን እንደ ሙሉ ደስታ መቁጠር እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ይህ ደግሞ በፈተና አልፈን እንድንጠነክር የሚያደርገን ነው። (1 ጴጥ. 6-7፤ ያዕ. 2-3) ነገር ግን በአባትያችን ሆይ ጸሎት “ወደ ፈተና አታግባን” ብለን ስንጸልይ የምንጠይቀው በክፉ ምኞት አጥምዶ ወደ ኃጢያት ከሚወስደው ፈተና እግዚአብሔር እንዲጠብቀን ነው። የጸሎቱ ሃሳብ ጸጋን ማለትም የእግዚአብሔርን ጥበቃ መጠየቅ ነው። አባታችን ሆይ ወደ ፈተና አታግባን። አሜን!